# ፈጣን የኤች.አይ.ቪ. መመርመሪያ ኪቶች የፍተሻ እና ግምገማ ጥናት እና የብሔራዊ ኤችዃአይ.ቪ. ምርመራ አልጎሪዝም ምሥረታ ሂደትና ውጤቶች

## 1. መግቢያ

ሀገራችን UNAIDS ያስቀመጠውን የሶስቱን 90-90-90ዎች እቅድ በመተግበር በ2030 ስርጭቱን ለመግታት እየሠራች ትገኛለች፡፡

የመጀመሪያው 90 ግብ ለሁሉም የኤች.አይ.ቪ. የመከላከያ፣ የሕክምናና የክትትል መግቢያ በር ነው፡፡ይህም ግብ በአንድ አገር ውስጥ ይኖራሉ ተብለው ከሚታመኑት የቫይረሱ ተሸካሚዎች ዘጠና በመቶዎቹ በላቦራቶሪ ተመርምረው በእርግጥም ተሸካሚ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ የሚል ነው ፡፡

በዛሬው ጊዜ በገበያ ላይ ያሉ ፈጣን የኤች.አይ.ቪ. መመርመሪያ ኪቶች በተለይም በዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ተፈትሸው ቅድመ ዕውቅና ያገኙት የቫይረሱን በሰው ደም ውስጥ መኖርና አለመኖርን የማረጋገጥ አቅማቸው እጅግ በጣም አስተማማኝ ነው፡፡ይሁን እንጂ ሁሉም ኪቶች በተለያዩ አህጉራት፣አገራትና አካባቢዎች ሊኖሩየሚችሉትን የቫይረሱን ዝርያዎች በእኩል ደረጃ የማግኘት አቅማቸው ውስኑነት አለው፡፡

ስለሆነም የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት እነዚህንና ሌሎች የፈጣን ኤች.አይ.ቪ. መመርመሪያ ኪቶች ውስንነቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በእነዚህ የሚከናወኑ ምርመራዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክረ-ሃሳቦች ላይ መመሥረት እንዳለባቸው ጉዳዩን አስመልክቶ በተለያዩ ወቅቶች ባወጣቸው ሪፖርቶች /በተለይም የ2015ቱ ሪፖርት ቁጥር 18/ ውስጥ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

1. ፈጣን የኤች.አይ.ቪ. ምርመራዎች በቁጥር ከሦስት ባላነሱ የተለያዩ ኪቶች ጥምረት ወይም አልጎሪዝም መከናወን እንዳለባቸው፤
2. በአልጎሪዝሙ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ኪቶችም በአገር ውስጥ ጥናት ተፈትሸውና ተገምግመው ቫይረሱ ያለባቸውን ከሌለባቸው በእርግጠኝነት የመለየት አቅማቸውና በተጨባጭ ከአገራዊ የምርመራው አገልግሎት አሰጣጥ ሥርጭት አንፃር ተስማሚ የአጠቃቀም ባህሪያት እንዳሏቸው ማረጋገጥ፤

ኢትዮጵያ በታሪኳ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ያወጣቸውን መመሪያዎችና ያስቀመጣቸውን ምክረ-ሃሳቦች ተከትላ ብሔራዊ ፈጣን የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አልጎሪዝም ያዘጋጀችውና የተገበረችው ሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን በመጀመሪያው Determine, Capillus እና Uni-Gold የተባሉ ኪቶች በተቀመጠው ዝርዝር ቅደም ተከተል መሠረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃዎች መመርመሪያነት የተጣመሩበት ነበር፡፡ ለሁለተኛ ጊዜም በ2007 ዓ.ም በተከናወነው ብሔራዊ የኪቶች ፍተሻ ጥናት KHB ፣ Stat-Pak እና Uni-Gold ተመርጠው በተቀመጠው ዝርዝር ቅደም ተከተል መሠረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃዎች መመርመሪያነት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡

ይሁን እንጂ ተከትሎ መከናወን የነበረበት ብሔራዊ የፍተሻና ግምገማ ጥናት በተለያዩ ምክንያቶች በመስተጓጎሉና በመዘግየቱ እንዲሁም በ1ኛ መመርመሪያነት በጥቅም ላይ የነበረው KHB ሳይጠበቅ በቅጽበት በዓለም ጥና ጥበቃ ድርጅት አገልግሎት ላይ እንዳይውል በመታገዱ ምክንያት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው የምርመራ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ሲባል የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት በጥራታቸው ቅድመ ዕውቅና ከሰጣቸው ውስጥ በዋጋ ብቻ ተወዳድረው እንዲገዙ በተደረገው መሠረት በመጀመሪያ ግዢ Frist response, Uni-Gold እና Vikia በሁለተኛው ደግሞ Beijing Wantai, Uni-Gold እና Vikia ወደ አገር ውስጥ ገብተው በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሠረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ መመርመሪያነት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ በሁለተኛ ዙር የግዢ ሂደት የተመረጡት Beijing Wantai, Uni-Gold እና Vikia የአገሪቱ የሽግግር አልጎሪዝም ሆነው ቀጥለዋል፡፡

ከላይ በሰፊው እንደተብራራው አንድ አገር ደረጃን የጠበቀ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አገልግሎት መስጠት ይችል ዘንድ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ያወጣቸውን መመሪያዎችና ያስቀመጣቸውን ምክረ-ሃሳቦችን ተከትሎ ብሔራዊ የፍተሻ ጥናትና ግምገማ በማካሄድ ተስማሚ ኪቶችን መርጦ ብሔራዊ የምርመራ አልጎሪዝም በሥራ ላይ ማዋል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማም ይህንን ትልቅ ክፍተት ለመሙላትና በአሁኑ ጊዜ በሽግግር አልጎሪዝም እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ዓለም አቀፍ መሥፈርቶችን ባሟላ መልኩ እንዲሰጥ ለማድረግ ነው፡፡

## 2. የፍተሻና ግምገማ ጥናቱ ዋነኛ ተግባሮች

1. በተለያዩ ፈጣን የኤች.አይ.ቪ. መመርመሪያ ኪቶች ላይ የፍተሻና ግምገማ ጥናት በማካሄድ ለኢትዮጵያ የሚስማማ አንድ ወጥ አልጎሪዝምና አማራጭ አልጎሪዝሞችን ማስቀመጥ

2. ለዚሁ የፍተሻ ጥናትና ለሌሎች የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች የሚያገለግል ባዮባንክ መመሥረት

## 3. የፍተሻና ግምገማ ጥናቱ ዘዴና ግብዓቶች

### 3.1 የብሔራዊ ግብረ-ኃይል ምሥረታ

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፍተሻና ግምገማ ጥናቱ ሂደት ግልፀኝነትን የተላበሰ፣ ከማናቸውም ሊከሰት ከሚችል አድሎአዊነት የነፃ ሆኖ ታአማንነትና በሁሉም ተቀባይነት ያለው ውጤት ያስገኝ ዘንድ ከነበረው ከፍተኛ ፍላጎት ለጉዳዩ ቅርበትና ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጅቱን ያላቸው ዓለም አቀፍ አጋር ድርጅቶችና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተመረጡ ኤጀንሲዎች የተወከሉበት ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም አድርጓል። በዚህም መሠረት የሚከተሉት ድርጅቶች በብሔራዊ ግብረ-ኃይሉ እንዲወከሉ የተደረገ ሲሆን የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትም ግብረ-ኃይሉን እንዲያስተባብርና እንዲመራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

1. የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የላቦራቶሪ ኤክስፐርቶች
2. የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኤች.አይ.ቪ. ኘሮግራም አስተባባሪ
3. የፌዴራል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ተወካይ
4. የአይ.ካፕ ኢትዮጵያ (ICAP) ተወካይ
5. የኢትዮጵያ የምግብ፣መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ተወካይ
6. የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት የአገር ውስጥ ቢሮ ተወካይ (WHO)
7. የተባበሩት መንግሥት የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ኘሮግራም የአገር ውስጥ ቢሮ ተወካይ (UNAIDS)

8. የሲ.ዲ.ሲ. ኢትዮጵያ ተወካይ (CDC-Ethiopia)

9. የአሜሪካን እርዳታ ድርጅት የአገር ውስጥ ቢሮ ተወካይ (USAID)

10. የክሊንተን ሄልዝ አክሰስ ኢንሼቲቭ ተወካይ (CHAI)

ብሔራዊ ግብረ-ኃይሉም የተቋቋመበትን ተልዕኮ መሠረት በማድረግ የሥራ ዝርዝር ቢጋሩን አዘጋጅቶ ካፀደቀ በኋላ ወደ ሁለት መሠረታዊ ሥራዎች የተሸጋገረ ሲሆን እነዚህም ለፍተሻና ግምገማ ጥናቱ የሚያስፈልገውን ኘሮቶኮል ማዘጋጀትና የባዮባንክ መመሥረት ናቸው፡፡

## <u>3.2. የኘሮቶኮል ዝግጅት</u>

ብሔራዊ ግብረ-ኃይሉ እጅግ በጣም ረዥም ጊዜ በወሰደና ብዙ ጥልቅ ውይይቶችን ባስተናገደ ሂደት ጥናቱ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ያወጣቸውን መሥፈርቶችና መመሪያዎችን ባሟላ መልኩ እንዲካሄድ የሚያስችል ኘሮቶኮል አዘጋጅቷል፡፡ ኘሮቶኮሉንም በጣም የዳበረና ፍፁም የተሟላ ለማድረግ በመስኩ የላቀ ዕውቀት ያላቸው ምሁራን እንዲተቹት ከመደረጉም በተጨማሪ የሲ.ዲ.ሲ-አትላንታ፣ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅትና የክሊንተን ሄልዝ አክሰስ ኢኒሼቲቭ ዋና መሥሪያ ቤት የመስኩ ኤክሰፐርቶች እንዲገመግሙትና እንዲያጠናክሩት ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱ ሂደቶች ውስጥ አልፎ የተዘጋጀው ኘሮቶኮል በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሳይንስና ኢቲካል ግምገማ ጽ/ቤት (Scientific Ethical Review Office) ታይቶና ተገምግሞ እንዲፀድቅ በማድረግ ጥናቱ እንዲጀመር ዋነኛውን ቅድመ-ሁኔታ አመቻችቷል፡፡

## 3.3 <u>የባዮባንክ ምሥረታ</u>

የዚህ ጥናት አንኳር ጉዳይ የተለያዩ የፈጣን የኤች.አይ.ቪ. መመርመሪያ ኪቶችን በሰው ደም ውስጥ የቫይረሱ አንቲቦዲዎች ለመናራቸውና ላለመኖራቸው በትክክል የመለየት አቅም መፈተሸና መገምገም እንደመሆኑ መጠን የቫይረሱን አንቲቦዲዎች በእርግጠኝነት የያዙና ያልያዙ በቂ የሰው ደም ናሙናዎች መኖር ወሳኝ ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከብሔራዊ የደም ባንክ አገልግሎት ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት 263 ናሙናዎች ሊሰበሰቡ የቻሉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ

51ዎቹ በደም ባንኩ ላቦራቶሪ ምርመራ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲዎች እንዳላቸው ተረጋግጦ የተቀሩት 212 ናሙናዎች ደግሞ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲዎች ሳይኖራቸው በጥቅም ላይ እንደውሉ የተደረጉ ነበሩ፡፡ የእነዚህን ናሙናዎች ሁለንተናዊ ባህሪያቶችን በሰፊው ለማስተንተንና እርግጠኛ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲ ይዘታቸውን መቶ በመቶ ለማስተማመን ሲባል ወደ ሲዲሲ አትላንታ ተልከው በድርጅቱ ሴሮሎጂ ላቦራቶሪ መጠነ ሰፊ ምርመራዎች የተከናወኑባቸው ሲሆኑ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲ ይዘታቸውም በድጋሚ በማያጠራጥር ሁኔታ ሊረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት መመሪያዎችና ምክረ-ሃሳቦች መሠረት የተያዘውን ጥናት ዓይነት ለማከናወን ቢያንስ 500 የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲ ይዘታቸው በትክክል የተረጋገጠላቸው ናሙናዎች ስለሚያስፈልጉ ከኢትዩጵያ ከተገኙት በተጨማሪ 88 የቫይረሱ አንቲቦዲ የሌለባቸውና 149 የቫይረሱን አንቲቦዲዎች የያዙ ናሙናዎች ከሲዲሲ አትላንታ ሴሮሎጂ ላቦራቶሪ በትብብር መልክ ተገኝተው ባዮባንኩ በጠቅላላው በ200 የቫይረሱን አንቲቦዲ በያዙና 300 የቫይረሱን አንቲቦዲ በሌላቸው ደረጃን በጠበቁ ናሙናዎች ሊደራጅ ችሏል፡፡

### 3.3. ኪቶችን ለመሰብሰብ የወጣ ግልጽ የሕዝብ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ለፍተሻና ግምገማ ጥናት የሚውሉ የተሟሉ እና 800 ምርመራዎችን ማድረግ የሚያስችሉ የመመርመሪያ ኪቶች አቅራቢዎች/አምራቾች እንዲያስገቡ በድረ ገጾች እንዲሁም በአዲስ ዘመንና በሄራልድ ጋዜጣ ማስታወቂያ አወጣ፡፡ የመመርመሪያ ኪቶቹ በግምገማው ሂደት ለመሳተፍ የሚጠበቅባቸው መስፈርቶች እንደሚከተሉት ተጠቅሰዋል፡፡

1. ከአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት የጥራት ቅድመ እውቅና ወይም Global Fund ዝርዝር ውስጥ መሆን
2. የተሟላ ማለትም ቢያንስ የመጠቀሚያ መመሪያ፣ መርፌ፣ የአልኮል መጥረጊያ ናሙና ማሸጋገሪያ ቁስ እንዲሁም የመጠቀሚያ ጊዜ ቢያንስ 12 ወር መሆን
3. ከአቅራቢዎች ከአምራቾች የውክልና ሰነድ ማቅረብ መቻል ሲሆን ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ30 ተከታታይ ቀናት የመመርመሪያ ኪቶቹ ማስገባት የሚሉ ሲሆኑ ሁሉም በዚሁ በተሰጠው ቀን አስገብተዋል፡፡

በአጠቃላይ ኢንስቲትዩቱ ዘጠኝ የመመርመሪያ ኪቶችን ለቅድመ ላቦራቶሪ ምርመራ ተረክቧል፡፡ ሁሉም መመርመሪያዎች በኮድ እንዲታወቁ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ፈጣን መመርመሪያ ኪት 1-9 ተብለው ተሰይመዋል፡፡ ይህም በምርመራ ወቅት የነበሩትን ውጤቶች የሚያፀድቅ ግብረ-ኃይል የትኛው የመመርመሪያ መሣሪያ እንደሆነ እንዳያውቅ ሲሆን ምርመራውን በበቂ ውጤት ያለፉትና ያላለፉት ከተለዩ እና ከፀደቁ በኋላ/ሪፖርቱ ካለቀ በኋላ/ ኪቶቹ በብሔራዊ ግብረ-ኃይሉ ፊት ይፋ ሆኗል፡፡ ከዘጠኙ  ሰባቱ በማስታወቂያው መሠረት ለላብራቶሪ ፍተሻ ለመቅረብ ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ ሁለት የመመርመሪያ ኪቶች በወጣው ማስታወቂያ መስፈርቶች መሠረት የተሟሉ ስላልነበሩ ወደ ላቦራቶሪ ፍተሻው ማለፍ አልቻሉም፡፡

እያንዳንዱ የተቀሩት ሰባት ኪቶች ግን በጥናቱ ውስጥ ተካተው 200 የቫይረሱን አንቲቦዲዎች የያዙ ናሙናዎችን በርግጥም መያዛቸውን የማሳየት ባህርያቸው /አቅማቸው/ (Sensitivity) እና 300 የቫይረሱን አንቲቦዲዎች ያልያዙ ናሙናዎች በርግጥም አለመያዛቸውን የማመልከት አቅማቸው/ባህሪያቸው (specificity) በጥብቅ የላብራቶሪ ምርመራዎች እንዲፈተሽ ተደርጎ

## 3.4 <u>የጥናቱ ወቅት/ጊዜ</u>

ጥናቱ የተጀመረው በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም ውስጥ ሲሆን የላቦራቶሪው ሥራ ከግንቦት እስከ ሰኔ 2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተከናውኗል፡፡

## 3.5. <u>ጥናቱ የተጠቀባቸው የናሙና ብዛት፡-</u>

ጥናቱ ቀድመው በሲ.ዲ.ሲ. አትላንታ ላቦራቶሪ የተረጋገጠ 200 የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲዎች የያዙ እና 300 የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ አንቲቦዲዎች የሌለባቸው በአጠቃላይ 500 ናሙናዎችን ተጠቅሟል፡፡

### 3.6 <u>የምርመራው ሁኔታ</u>

ምርመራው የተካሄደው በአንድ የላቦራቶሪ ቦታ ሲሆን ሁሉም መመርመሪያ ኪቶች በሁለት መርማሪና በሶስቱ አንባቢዎች ተሠርቷል፡፡ የክፍሉ የአየር ሁኔታና የናሙናዎቹ አቀማመጥ በየቀኑ የሚታዩና የሚመዘገቡ ነበሩ፡፡ መርማሪዎቹና አንባቢዎቹ በቀን መሥራት የሚችሉትን ብቻ በተመሳሳይ የሥራ ሁኔታ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

### 3.7 <u>የምርመራው ጥራት ማረጋገጫ መንገዶች</u>

መርማሪዎችና አንባቢዎች በጥራት እንዲመረምሩና እንዲያነሱ የአንድ ሳምንት ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ የጥራት ተቆጣጣሪ ብሔራዊ ግብረ-ኃይሉ አባላት /በኢ.ህ.ጤ.ኢ፣ ሲ.ዲ.ሲ፣ ቻይ

እና አይካን የተውጣጡ መርማሪዎች፣ አንባቢዎች እና ሌሎች በማንኛውም ሁኔታ ከሂደቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሁሉ የሂደቱንና የመመርመሪያውን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ቃል የተገባበት ቅጽ ፈርመዋል፡፡ ጠቅላላና ዝርዝር የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቶ በሁሉም መርማሪና አንባቢ ተነቦና ተፈርሞ ወደ ሥራው ተገብቷል፡፡

## 4. ለብሔራዊ ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አልጎሪዝም የቀረቡ የኪቶች ጥምረት አማራጮች

በላቦራቶሪ ጥልቅ ምርመራ ከተደረገባቸው ሰባት ኪቶች መካከል አራት ኪቶች የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ካስቀመጣቸው የጥራት መሥፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ ባህሪያት በማሳየት ተቀባይነት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ አራቱም ኪቶች Vikia HIV ½ (BioMeneux), Abon HIV 1/2/0 (Abone Biopharm), SD Bioline HIV ½ 3.0 (Standard Diagnostics) እና HIV ½ Stat-pak (Chembio) ከሞላ ጎደል እኩል ወይም የተመጣጠነ የቫይረሱን አንቲቦዲዎች ያላቸውንና የሌላቸውን በእርግጠኝነት የመለየት አቅም አሳይተዋል፡፡

ከሰባቱ ሶስቱ ኪቶች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የጥራት መመዘኛ መሥፈርቶች የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ያስቀመጠችውን ደረጃዎች ሚሟላት ስላልቻሉ ወይም በአላመቺ የአጠቃቀም ባህሪያቸው ጥራት ያለውና አስተማማኝ ውጤት ለመስጠት የማያስችሉና እስከተሳሳተ ውጤት ክስተት ሊዳርጉ የሚችሉ ሆነው በመገኘታቸው ከኪቶቹ ጥምረት ምሥረታ ውጪ እንዲሆኑ ተወስኗል፡፡

ስለሆነም ይህንን ጥናት በበላይነት የመራው ብሔራዊው ግብረ ኃይል ከላይ በጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመሠረትና የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ያስተላለፍቸውን ምክረ-ሃሳቦች በጥንቃቄ በመከተል የሚከተሉትን ውሳኔዎች በአንድ ድምጽ አስተላልፏል፡፡

1. First Response HIV 1/2/0 (Premier Medical Corporation) ፣ Insti HIV-1/HIV -2 (BioLytical እና Collodial Gold (Beijing Wantai) በዚህ ጥናት ውጤቶች ላይ ተመሥርቶ በሚዘጋጀው ብሔራዊ የኤች አይ ቪ ምርመራ አለጎሪዝም ውስጥ እንዳይካተቱ
2. Abon HIV 1/2/O (Abon Biopharm ) ፣ SD Bioline HIV ½ 3.0 (Standard Diagnostic) እና HIV ½ Stat-Pak (Chemibio) ለወደፊት በሚዘጋጅ ብሔራዊ የኤች አይ ቪ ምርመራ አልጎሪዝም ውስጥ ሊካተቱ እንደሚችሉና ማናቸውም በማንኛውም ጊዜ በግዥ ሂደት በዋጋ መበላለጥ ብቻ በሚወሰን ሁኔታ በአንደኛ ወይንም በሁለተኛ

ወይንም በሶስተኛ ደረጃ መመርመሪያነት ሊያገለግሉ እኩል እድል እንዳላቸው፡፡ የBiomerieuxው ኩባኒያ Vikia HIV ½ ካለው ረዥምየውጤት ጊዜ (30 ደቂቃ) እና ከሚፈለገው ከፍተኛ የደም መጠን ( 75 ማይክሮ ሊትር ) አንፃር ታየቶ በአንደኛ ደረጃ መመርመሪያነት መገልገል እንደማይችልና ሆኖም ግን በሁለተኛ ወይንም በሶስተኛ ደረጃ መመርመሪያነት ሊጠቀም እንደሚችል ፡፡

ከላይ የተዘረሩትን ውሳኔዎች መሠረት በማድርግ ለአንደኛ ፣ ለሁለተኛ ፣ ለሶስተኛ ደረ ጃዎች መመርመራያነት የሚችሉ የኪት አማራጮች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

1. ለአንደኛ ደረጃ መመርመሪያነት
   - Abon HIV 1/2/O (Abon Biopharm)

     ወይንም
   - SD Bioline (standard Diagnostics )

     ወይንም
   - HIV ½ Stat—Pak ( Chemibio)
2. ለሁለተኛ ደረጃ መመርመሪያነት
   - Abon HIV 1/2/O (Abon Biopharm)

     ወይንም
   - SD Bioline (standard Diagnostics )

     ወይንም
   - HIV ½ Stat —Pak ( Chemibio)

     ወይንም
   - Vikia HIV ½ (Biomerieux)
3. ለሶስተኛ ደረጃ
   - Abon HIV 1/2/O (Abon Biopharm)

     ወይንም
   - SD Bioline HIV ½ 3.0 (Standard Diagnostics )

     ወይንም
   - HIV ½ Stat —Pak ( Chemibio)

     ወይንም

- Vikia HIV ½ (Biomerieux)

እነዚህ አማራጮች የጤና ጥበቃ ሚ/ር በግዢ ሂደት ለያንዳንዱ ኪት በሚቀርበለት ዋጋ ላይ ተንተርሶ ተገቢውን የመመርመሪያ ደረጃ ይወሰን ዘንድ እንዲረዱ የቀረቡ ናቸው፡፡ ሶስቱ የኪት እይነቶች ከአንድ አስከ ሶስት ያሉትን የመመርመሪያ ደረጃዎች ከያዙ በኃላ የሚተርፈው ኪት ለችግር ጊዜ ማለትም አምራቹ ማምረት ቢያቆም ወይንም አንድ ኪት በጥራት መጓደል ምክንያት የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት የጥራት ቅድመ-እውቅና ቢነፈግ ወዘተ --- ለመጠባበቂያ የሚያዝ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም በተገለፀው መሠረት በሶስት ኪቶች ጥምረት በሚጋጀው አለጎሪዝም ውስጥ ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑት ምርመራዎች የዓለም ጤና ድርጅት በቅርቡ ዝቅተኛ ብሔራዊ የኤች አይ ቪ ስርጭት ባለበት ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ያወጣው የኤች አይ ቪ የመርመራ ስትራቴጂን በመከተል ይሆናል ፡፡ የስትራቴጂው ዋነኛ መገለጫ አንድ ተመርማሪ ቫይረሱ እንዳለበት የሚረጋገጠው በሶስቱም ኪቶች በቅደም ተከተል ተመርምሮ በሁሉም ፓዘቲቭ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡